ከአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት) የተሠጠ መግለጫ

# መንግሥት ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌዎችን

# እያከበረና እያስከበረ አይደለም!

መንግሥት ያወጣውን ሕገ-መንግሥት የማክበርና የማስከበር ኃላፊነት አለበት፡፡ ይህንን ኃላፊነቱን ግን በሚገባ እየተወጣ አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት የዜጎች መሠረታዊ መብቶች እየተጣሱ ነው፡፡

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ በሕጉ መሠረት ተመዝግቦና የምስክር ወረቀት ተሰጥቶት በሀገር አቀፍ ደረጃ በይፋ የሚንቀሳቀስ ፓርቲ ነው፡፡ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ቤቶችን ለመክፈት ወደ ክልሎች በአደረጋቸው እንቅስቀሴዎች ሁሉ የተሰጠውን የእውቅና የምስክር ወረቀት ትብብርን ከሚጠይቅ የፓርቲው ደብዳቤ ጋር ለሚመለከታቸው የክልል አካላት ሁሉ አቅርበናል፡፡ እያቀረብንም ነው፡፡ ሆኖም በተለያየ ደረጃ የሚገኙ አንዳንድ የክልል የመንግሥት ባለሥልጣናት ከምርጫ ቦርድ ለተሰጠው የምስክር ወረቀትም ሆነ ከፓርቲያችን ለተፃፈው የትብብር ደብዳቤ ዋጋ ባለመስጠት ቢሮዎቻችንን በመዝጋት፤ አባሎቻችንን በማሰርና በማስፈራራት፤ የጽህፈት ቤቶቻችንን ንብረቶች በማውደም፤ ለጽ/ቤቶቻችን ቤቶች ያከራዩንን ባለንብረቶች በማስፈራራት ውሎቻቸውን እንዲያፈርሱ ተጽእኖ በማድረግ ዘርፈ ብዙ ሕገ-ወጥ ድርጊቶችን እየፈፀሙ ነው፡፡ ይህንንም በማድረጋቸው የፓርቲያችን የመደራጀትና በነፃነት የመንቀሳቀስ ሕገ-መንግሥታዊ መብት እየተጣሰ ነው፡፡ ለአብነት ያህል ብቻ:-

***በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክላዊ መንግሥት*** በሳውላ ከተማ አመራሮችን ማሠር፤ በቦዲቲ (በወላይታ ዞን) ጽ/ቤታችንን መዝጋትን፤

**በኦሮሚያ ክልል** በሀገረ ማሪያም የጽ/ቤቱን ማንዲራ ወስዶ ማበላሸት እንዲሁም በመቱ የጽ/ቤቱን ተጠሪ ለሁለተኛ ጊዜ ማሠርን፤

**በአማራ ክልል** የደብረ-ማርቆስና ሌሎች ወረዳዎች ጽ/ቤቶችን መዝጋትና አመራሮችን ማሠር መጥቀስ ይቻላል፡፡

የድርጅታችን የወጣቶች ጉዳይ ሚዲያና ኮሚኒኬሽን ንዑስ ኮሚቴ አባላትና ደጋፊዎቻው የሚሳተፉበት የሥነ-ጽሁፍ ምሽት አዘጋጅተው ጥር 18 ቀን 2001 ዓ.ም የሚያካሂድ መሆኑን በአዲስ አበባ አስተዳደር ለሚመለከተው አካል በጽሑፍ አሳወቀ፡፡ የሚመለከተው ክፍል «በወቅቱ የአፍሪካ መሪዎች ጉባኤ የሚካሄድበት በመሆኑ ፕሮግራማችሁን ከስብሰባው በኋላ ብታካሂዱ» የሚል ሃሳብ በጽሑፍ ስለአስተላለፈልን ሃሳቡን በመቀበልና በማክበር ፕሮግራማችንን አስተላለፍን፡፡ ከመሪዎቹ ስብሰባ በኋላ ቀደም ሲል ያቀድነውን ፕሮግራም የካቲት 10 ቀን 2001 ዓ.ም እንደምናካሂድ የማሳወቂያ ደብዳቤ ቀደም ሲል ለተጠቀሰው የአዲስ አበባ አስተዳደር ክፍል ጥር 29 ቀን 2001 ዓ.ም አስገባን፡፡ ነገር ግን እስከአሁን ድረስ ተገቢው መልስ አልተሰጠንም፡፡ ለምን እንዳልተሰጠን ስንጠይቅ የተሰጠን መልስ «የሚለከታቸው ኃላፊዎች ውሳኔ አልሰጡበትም» የሚል

ነው፡፡ በሕጉ መሠረት የማሳወቂያው ሰነድ ከገባ በኋላ በ12 ሰዓት ውስጥ መልስ ካልተሰጠ የማሳወቂያው ማመልከቻው ተቀባይነት እንዳገኘ ተቆጥሮ የታቀደው ፕሮግራም ሊከናወን ይችላል፡፡

ሆኖም በተደጋጋሚ የሚከሰቱ ሁለት ችግሮች አሉ፡፡ አንደኛው ችግር በ12 ሰዓት ውስጥ ከሚመለከተው አካል መልስ ካልተሰጠ ማመልከቻው ተቀባይነት እንዳገኘ ተቆጥሮ የታቀደውን ፕሮግራም ለማካሄድ ቢሞከር ፖሊስ በቦታው ተገኝቶ «ፈቃድ የላችሁም» በማለት ፕሮግራሙ እንዳይካሄድ ያግዳል፡፡ በዚህ መብት ለማስከበር በሚፈጠር ክርክር አላስፈላጊ ግጭት ሊፈጠርና ጉዳት ሊደርስ ይችላል፡፡

በሌላ በኩል የመሰብሰቢያ አዳራሽ የሚያከራዩ ድርጅቶች ከሚመለከተው የመንግሥት አካል የመሰብሰቢያ «ፈቃድ» ካላመጣችሁ አናከራይም ይላሉ፡፡ ለምን ተብለው ሲጠየቁ «ፈቃድ» ለሌለው ድርጅት እንዳናከራይ መመሪያ ተሰጥቶናል ይላሉ፡፡ መመሪያው ከማን እንተሰጣቸው፤ በምን መልክ እንደተሰጣቸውና መቼ እንደተሰጣቸው ሲጠየቁ ግን ለመናገር ፈቃደኞች አይደሉም፡፡ በዚህ መሀል የታቀደ ጠቃሚ ፕሮግራም ሳይካሄድ ይቀራል፡፡ በዚህ መሀል አንድ በሕግ የተቋቋመ የፖለቲካ ድርጅት ለአባላቱና ለደጋፊዎቹ ጠቃሚ ፕሮግራም የማካሄድ መብቱ በአስተዳደራዊ ስልት ይጣሳል፡፡ ይህ ድርጊት የሕግ ጥሰትና የአስተዳደር ድክመት ብቻ አይደለም፡፡ ከበስተኋላው የአንድነትን እንቅስቃሴ ለመገደብና ከሕዝብ ጋር የመገናኘት እድሉን ለማጥበብ ታቅዶ የሚከናወን የፖለቲካ ተግባር ነው፡፡

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት) ሊቀመንበር ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሣ ዳግም መታሰርም በሕግ ጥሰት የታጀበ ነው፡፡ እዚህ ላይ አንድ ነገር ግልጽ መሆን አለበት፡፡ ይኸውም በተደጋጋሚ እንደተገለፀው አንድነት ሕግ የጣሰ ሰው በሕግ መጠየቅ የለበትም የሚል አቋም የለውም፡፡ የአንድነት አቋም ግን በህግ የመጠየቅ ሂደቱ ራሱ ሕግን የተከተለ መሆን አለበት የሚል ነው፡፡ ከዚህም አቋም በመነሳት ይህች አገር የምትተዳደረው በሕግ ከሆነ የወ/ት ብርቱካን ለዳግም እስራት መዳረግ ሕግን የተከተለ አይደለም የሚል ጽኑ እምነት አለው፡፡

ወ/ት ብርቱካን በመጨረሻ የጽሑፍ ቃላቸው የኢትዮጵያ ሕዝብንና መንግሥትን ይቅርታ ጠይቀዋል፡፡ ስለዚህ ይቅርታ አልጠየቁም በሚል ቀደም ሲል የተሰጠ ይቅርታ ያለበቂ ምክንያት ሊነሳ አይገባም፡፡ መነሳት ካለበት ደግሞ አነሳሱ ሥርዓት አለው፡፡ ይህም ሥርዓት በአዋጅ ቁጥር 395/1996 ተደንግጓል፡፡ ወ/ት ብርቱካን ለእስር የተዳረጉበት ሂደት በዚህ አዋጅ ውስጥ የሰፈሩ ድንጋጌዎችን ይጥሳል፡፡ ለምሳሌ የአዋጁ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ይህን ይደግፋሉ፡፡

ወ/ት ብርቱካን እንደገና የታሰሩበትን ጉዳይ በተመለከተ በጽሑፍ የተሰጣቸው ሠነድ የለም፡፡ እስካሁንም የደረሳቸው ሠነድ የለም፡፡ ለእድሜ ልክ እስራት መዳረግ ቀላላ ጉዳይ ባለመሆኑ ለታሪክ መመዝገብም ስለአለበት የጽሁፍ ሠነድ መኖርን ግድ ይላል፡፡ ይቅርታው የተሰጠው ለምን

እንደተሰጠ በሚገልጽ ጽሁፍ ነውና ሲነሳም ለምን እንደተነሳ በሚገልጽ ጽሑፍ መሆን አለበት፡፡ በሌላ በኩል ይቅር ተባዩ ይቅርታው ለምን እንደሚነሳ በሑፍ ከደረሰው በኋላ የአዋጁ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 2 ከሃያ ቀን ያልበለጠ ጊዜ ይሰጠዋል ይላል፡፡ ወ/ት ብርቱካን ይህ መብታቸው አልተከበረላቸውም፡፡ ሙሉ ይቅርታ ተደርጎለት ከነሙሉ መብቱ ከእስር የተፈታ ሠላማዊ ዜጋ ያለፍርድ ትእዛዝ እንደማይያዝና ለእስር እንደማይዳረግም ሕጉ ይደነግጋል፡፡ ወ/ት ብርቱካን ወደ ወህኒ የተወሰዱበት ሁኔታ ግን ከጎዳና ላይ ሰብአዊ መብታቸውን በሚነካ ሁኔታና የመያዣ ትእዛዝ በጽሑፍ ሳይደርሳቸው ነው፡፡

ስለዚህ ቢያንስ በእነዚህ በተጠቀሱት የሕግ ጥሰቶች ምክንያት ቀደም ሲል የተሰጠው ይቅርታ የፀና ሆኖ ወ/ት ብርቱካን ከእስር እንዲፈቱ እንጠይቃለን፡፡

በወ/ት ብርቱካን ጉዳይ ላይ ጠ/ሚኒስሩን ጨምሮ ሌሎች ባለሥልጣኖች በመንግሥት ሚዲያዎች ወደ አንድ ጎን ያጋደለ «ማብራሪያ» ሲሰጡ አስተውለናል፡፡ የመንግሥት ሚዲያ የጋራ መሆኑ ታምኖበት እኛም እድሉ ቢሰጠን ለማብራራት፤ ለመከራከር ዝግጁ መሆናችን በዚህ አጋጣሚ ጥሪ እናደርጋለን፡፡

በአሁኑ ጊዜ የማዕከልም ሆነ የክልል ባለሥልጣናት ሕግን በመጣስ የሚያሳዩት ድፍረትና ማንአለብኝነት በዚህች ሀገር የሕግ የበላይነት አለመከበሩን በግልጽ ያሳያል፡፡ መንግሥት በማዕከልም ሆነ በክልል ባለሥልጣናቱ አማካይነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የአንድነትን እንቅስቃሴ ለመገደብ የተቀነባበረ ዘመቻ የሚያካሂድበት ምክንያት ግልጽ ነው፡፡

የ2002 ሀገር አቀፍ ምርጫ እየመጣ ነው፡፡ ገዢው ፓርቲ አንድነትንም ሆነ ሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎችን አዳክሞ ብቸኛ ጠንካራ ፓርቲ ሆኖ ለመውጣትና በምርጫው አሸንፎ የሥልጣን ዘመኑን እንደተለመደው ለማራዘም ይፈልጋል የሚል እምነት አለን፡፡ ይህንን ግቡን ለማሳካትም የፈለገውን እርምጃ ለመውሰድ ሕግ እንደማይገታው እስካሁን ድረስ የወሰዳቸው የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ማስረጃዎች ናቸው፡፡

አንድነት በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ እንዲሰፍን፤ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት እውን እንዲሆንና የሕግ የበላይነት እንዲከበር ሠላማዊ ትግሉን አጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ ይቀጥላልም፡፡ በመንግሥት በኩል ግን ከላይ እንዳብራራነው ሕግን የማክበርና የማስከበር ኃላፊነቱን እየተወጣ ባለመሆኑ ይህንኑ ግዙፉ ኃላፊነቱን በተሟላ ሁኔታ እንዲወጣ አበክረን እንጠይቃለ፡፡

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)
የካቲት 19 ቀን 2001 ዓ.ም
<u>አዲስ አበባ</u>

ቁጥር፡ አንድነት 89/2001

ቀን፡ 17/2001 ዓ.ም

# ለኢትዮ-ቻናል ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ
# አዲስ አበባ

<u>ጉዳዩ፡- በ15/06/2001 ዓም በጋዜጣችሁ ስለፓርቲያችን የፃፋችሁትን ይመለከታል፤</u>

በተጠቀሰው ቀን የወጣው የጋዜጣችሁ ህትመት በግንባር እንዲሁም በገጽ 7 እና 8 «አንድነትና ግንቦት 7 ፓርቲ- በአንድ እጅ መስቀል በአንድ እጅ ሰይፍ» በሚል ስለፓርቲያችን ሰፋ ያለ ሀተታ አቅርባችኋል፡፡ ጋዜጣችሁ ተመሣሣይ ሀተታዎችን በተከታታይ እያቀረበ እንደሆነ ማንም አይስተውም፡፡ ከላይ የተጠቀሰው ሀተታም እንደተለመደው የነቀፋውና የውንጀላው ኢላማ የሆነውን የፓርቲውን ማስተካከያ (ማስተባበያ) ያልጋበዘና ሚዛኑን ያልጠበቀ ያንድ ጎን ጽሁፍ ነው፡፡

ፓርቲያችን የጋዜጠኝነትን ሙሉ የመፃፍ ነፃነት መብት መቀበል ብቻ ሣይሆን ሌሎች እንዲቀበሉት ግንባር ቀደም ሁኖ የሚታገል መሆኑ ይታወቃል፡፡

በዚህ እምነታችንና ጋዜጣችሁም እራሱን አስተካክሎ ፤ ለመርህና ለህግ ተገዝቶ ይመለሳል በሚል እሳቤ ለእያንዳንዱ አፍራሽ ሀተታ ምላሽ መስጠት ወይም ሌላ እርምጃ መውሰድ እንደአማራጭ ሳንወስድ ቆይተናል፡፡ አሁንም ትትክለኛ መረጃን ሚዛኑን በጠበቀ መልኩ እንደምታቀርቡ ተስፋ በማድረግ የሚከተሉትን ነጥቦች በጋዜጣችሁ ላይ እንድታቀርቡ እናሳስባለን፡፡

«ከፓርቲው ከፍተኛ አመራር አባል የተላከ በሚል እንደፃፋችሁት፡-

- የሠላማዊ ትግልንና የጦረኝነት ስልትን አጣምረንና አጣቅሰን የምንንቀሳቀስ አይደለንም፤ ለዚህም ጦር ከሰበቁ የተደራጁ ኃይሎች ጋር ስውር ዝግጅት እያደረግን አይደለንም፤
- ፓርቲያችን ህጋዊና ሠላማዊ በመሆኑ ሥራዎችን የሚሠራውም ሆነ የሚሰበሰበው በራሱ ጽ/ቤቶች ውስጥ እንጂ በየሆቴሉና በየግለሰቦች ቤት አይደለም፤
- ጥቃቅን ሀቅ መሣይ ነገሮችን ቀንጭቦ ከግዙፍ ሀሰቶች ጋር በመቀላቀል "ከውስጥ አዋቂ" ፤ "ከከፍተኛ የአመራር አካል" ፤ ወዘተ እያሉ የሚጽፉ የአፍራሽነት ተልእኮ አንግበው ከውስጣችን መወሸቃቸውን ብንጠረጥርም በፓርቲው አመራር አካላትና በአባላት መካከል የተፈጠረ መከፋፈልና ትርምስ የለም፤
- አንድነት በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ቅርንጫፎቹ የሚወክሉት ብቁ አባላት አጥቶ አያውቅም፤ ስለዚህም የሌላ ፓርቲ አባል (የግንቦት 7 ወይም የሌላ) በጥምር እንዲወክሉት ፈቅዶ አያውቅም፤ ለወደፊቱም አይፈቅድም፡፡
- የፓርቲያችን መሪ የሆኑት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሣ "የተሰጣቸው ይቅርታ ተነስቶ" እንደገና ወህኒ የገቡበት የህግ አግባብም ሆነ የተፈፀመበት ሥነ-ሥርዓት ትክክል አለመሆኑን አሁንም አስምረንበት ትግል እያካሄድንበት ያለ አንገብጋቢ ጥያቄ እንጂ ተቀብለን የተቀመጥንበት ሁኔታ ላይ አይደለንም፡፡

- ፓርቲያችን ሠላማዊ ትግልን ተቀብለው ከሚንቀሳቀሱ፤ ከፓርቲያችን መርህና ስትራቴጂ ጋር ከሚቀራረቡ ሌሎች ፓርቲዎች ጋር ግንባር፤ ህብረት፤ ወይም ጥምረት መፍጠሩ ትክክል ነው ብሎ ያምናል። በአሁኑ ወቅት በመድረክ ስም ከተሰበሰቡት ሌሎች ፓርቲዎች ጋር እንደሁኔታው የምናደርገው ግንኙነትና አብሮ መሥራትም በዚህ መልክ ተቃኝቶ በተገቢው የፓርቲው አመራር አካል የተወሰነበት እንጂ የጥቂት ግለሰቦች አምባገነናዊ ውሳኔ አይደለም።

በመጨረሻም መላው አባላትና ደጋፊዎቻችን ከልህ አስጨራሹ የሠላማዊ ትግል ስልት ጋር ላለመነጣጠል በቁርጠኝነ የወሰንን መሆኑን መስካሪው ተግባራችንና እናንተው ራሳችሁ መሆናችሁን አውቃችሁ ለማንኛውም አሉባልታ (የጋዜጣ ላይም ሆነ የሌላ) ጆሮ ላለመስጠት እንድትተባበሩን በአንክሮ ማሳሰብ እንወዳለን።

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ (አንድነት)
የሕዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ
<u>አዲስ አበባ</u>